ሐዋርያ- ቅጽ 13፤
ቁ. 2
ሰኔ/ሐምሌ 2000 ዓ.ም

# ርዕሰ አንቀጽ

## "ዐባይ አንተ ያየኸኝ ከደረት÷ እኔ ያየውህ ከጉልበት"!

መድሃኒት ገና ያልተገኘለት÷ እንዲያውም የወደፊት ግኝቱ ጭራሽ 'በዚህን ወይም በዚያን ጊዜ' ይሆናል ተብሎ የማይተነበይለትና ለሰው ልጅ ቀሳፊ በሽታ ከሆኑት ጠንቆች አንዱ÷ ማንአህሎኝነት ወይም የትእቢት እብጠት ነው:: የዚህ ደዌ ክፉነቱ ደግሞ÷ እየመረጠ የሚቀስፈው ቢሰነብቱ ለሕዝብና ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ዐይን ወጊዎች መሆኑ ነው:: ደዌው ለአቅመ አዳምና አቅመ ሄዋን የደረሱ÷ ከጉብል እስከ አዛውንት የሚጠናወት ሲሆን÷ ይህ በሽታ የሚጀምራቸው ሰዎች ከሚለዩባቸው ምልክቶች አንዱ÷ በሕዝብ ፊት ለሕዝብ "ቆመው" ሰው እየመረጡ ማስጣትና ማንጓለል ይጀምራሉ፤ ማበጠር የቻሏቸውን ጥቂት ሰሎዎች 'ጥሩ' ሲሉ÷ ተንጓሎ አልለይ ያላቸውን እምቅ ፍሬ ደግሞ 'ግርድ' ብለው ይበትናሉ:: ይሁን እንጅ ያ የናቁትና የደፉት ደቃቅ ምልአት ፍሬ÷ በበተኑበት ለም መሬት ላይ ከመቅጽበት ቱግ ብሎ በመብቀል÷ መሬት ውስጥ በተቀበሩ ህልው ሥሮቹ መጋቢነት ለምልሞ ያብባል:: የቡቃያው ሥር ቅጠልም ለመርዘኞች ፍቱን መድሃኒት ስለሚሆን÷ በቀመሱት ቁጥር በቁማቸው ሰርክቶ ይገድላቸዋል:: በዚህም አሟሟታቸው የከፋ ይሆናል::

ይህ የምርጦች ተላላፊ በሽታ እንዴት እንዴት ያሉ ቀናዊያንን እየነደፈ በሚያናውዝበት ወቅት÷ የህሙማኑ የቅርብ ወዳጆች በሽተኞቹ ብዙሃኑን ሳይበክሉ በቶሎ እንዲወገዱ ቢተባበሩባቸው እንጅ÷ በሥርዓተ ቀብራቸው ላይ ቆመው ዘለሳ እምባ እንኳ አያፈሱላቸውም:: ይልቁንስ÷ በሽታው ከፍተኛ የሕዝብና የሀገር ሃላፊነትን ሊሸከሙ በሚችሉ ክቡራንና ክቡራት ላይ ተላላፊ ስለሆነ÷ ሽግሪያውን ሕዝብ ነቅቶ እንዲከላከልና ከልክፍተኞች እንዲርቅ አስቸኳይ ጥሪ ይቀርብለታል::

ጠባብነት የጎዳንን ያክል÷ ትምክህተኛ ግለሰቦችም÷ በግልም ሆነ በቡድን ደረጃ በየፖለቲካ ድርጅቶችና በህብረተሰቡ ውስጥ እያቆጠቆጡ÷ በስንት የጋራ ጥረትና መስዋእትነት የተጋመደውን የብዙሃን ታሪክ ለመበጠስ ክፉኛ ጥረዋል:: ብዙ አጉራዘለል ቀብራሮች÷ በተፈጥሮ ያልታደላቸውን ሃይልና ጥበብ ተክነናል ብለው ስለሚገምቱ÷ የማይፈቀድላቸውን ለማድረግ በመሞከራቸው÷ የጎረሱትን ሳይውጡ እየታነቁ አልቀዋል:: እነዚህ ግብዝ ወገኖች ምን ጊዜም ሊረዱት ያልቻሉት ጉዳይ ቢኖር "ብዙሃኑን ሁልጊዜ ማታለል አይቻለም" የተባለውን ሃቅ ነው::

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአፋኙ አምባገነናዊ ሥርዓት የዕለት ተዕለት ፖለቲካዊ ውርጅብኝ ጀርባ÷ በከፍተኛ የማህበራዊና ምጣኔ-ሃብታዊ ማጥ ውስጥ መገኘቱ አሌ የማይባል ገሃድ ነው:: የሚገርመው ግን ለዚህ መጠነ ሰፊና ምስቅልቅሉ ለወጣ ችግር ምክንያቱና መሠረቱ ተፈጥሯዊና የዓለም አቀፉ ዘርፈ ብዙ ክስተት ጫና እንደሆነ አድርገው ሊያስረዱንና÷ በዚህም የችግራችንን መንስኤ ሥረ-መሠረት ምን ያህል እንደምናውቅ ሊገምቱን የሚሞክሩ መኖራቸው ነው:: ይህን መሰሉን ኩመካ ይሳካልናል ብለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያሳስቁ የሚጥሩት ደግሞ÷ ገዥዎቻችን ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ ሊያድሩ ያጎበጎቡና ለታማኝነታቸው ማጠየቂያ ጅራታቸውን የሚቆሉ ነውረኞች ጭምር ናቸው:: በአጽመ አካሉ በመኖር የመከራ ገፈቱን እየቀመሰ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ÷ ማን ይህን ሁሉ መዓት እንዳመጣበትና በላዩ ላይ እንደጫነበት አያውቅም ብሎ መዛበትና የዕውቀት ባህሩን በጭልፋ መለካት÷ ሌላው የንቀት አባዜያቸው ነው:: ለነገሩማ÷ በአንዳንዶች ፊት ሰፊው ባላገሩ ሕዝባችን ገና ያልሰለጠነና እንደ ልብሱ አዳፋነት ግምቱም የደበዘዘ አድርገው ነው የሚቆጥሩት:: በዚህም ግዙፍ ስህተት ይፈጽማሉ:: ቢያውቁበት ግን ብዙሃኑ ባላገር ሕዝብ ዘመናዊ ትምህርት ከቀሰሙት ልጆቹ የሚሻው ነገር ቢኖር÷ በረጅሙ ጥንታዊ ታሪኩ ያካበተውን÷ ቢዝቁት የማያልቅ ተመክሮውንና ነጥሮ የሚያበራውን በራስ የመተማመን ባህርይውን - ግንስ በጭንቅላቱ ተደፍቶ አልቆምልህ ያለውንና የብዙ ሺህ ዘመናት ዳዴውን - በእግሩ አቁመው ፈጥኖ ሲራመድበት ማሳየቱ ላይ ነው:: ጥቂት ተንሳፋፊዎች የብዙሃኑን ስም አንጠልጥለው አየር በአየር በመክነፍ÷ ልብሱ ከአደፈ÷ አነጋገሩ ከጎለደፈ በልጠነዋልና እንደፈለግነው ልንሠራው ይቻለናል ብለው ስለሚኳሹ÷ ከሕዝብ ሥነ-ልቦናና ከሀገር ጋር÷ ውሃና ዘይት የሆነውን ትእቢታችሁን ፈትሹ ሊባሉ ይገባል::

መቻልን ካላዋቂነት÷ ትእግስትን ከፍርሃት የሚቆጥሩና÷ ጥበባቸው ከበልባሊት ምላሳቸው የሚነትብ ዘመናዊያን÷ በስሙ የሚዥጎረጎሩበትን ይህን የራሱ የሆነ ክህሎት ያለውን ሕዝባችን÷ አንጡራ ማህበራዊ አደረጃጀቱንና አመለካከቱን ከሁሉም በፊት ሊረዱለትና ሊያውቁት ይገባል:: "ሰፊው ህዝብ" ብሎ ያልሰለጠነ ማለቱ÷ "ነጻ አውጭ" ነኝ ብሎ ነጻ ወጭውን አለማወቁ÷ እርባናው እውር-ድንብስ ሂደት ብቻ ሳይሆን መደምደሚያው ውድቅት ነው ሊሆን የሚችለው:: በዘመናዊው ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥረን ያለፍን ብዙዎቻችን÷ ጊዜና ሁኔታ አስገድዶን ተሰደን ስንኖር÷ በብዙው መልካችን ጉራማይሌ መሆናችን አይለጉት እጣ ፈንታችን ሆኖብን ሃፍረታችን መከናነባችን እርግጥ ነው:: ዳሩ ግን÷ ታሪክ ያለውን ሕዝባችን እንወክላለን ስንል÷ ስለሕዝቡና ስለሀገሪቱም አርአያ እንሆናለን ብለን ስንሰለፍ÷ መጀመሪያ ከተጠናወተን ግላዊ ስሜትና ዝብርቅርቅ አባዜ ራሳችን ነጻ ማውጣትና ሕዝባችን በአግባቡ አውቀን ተረድተን÷ "ከነንፍጥ ልጋጉ" መቀበል ግዴታችን መሆኑን ማወቅ ፈቅደን ለምንቀበለው ሃላፊነት መሠረት ነው:: ያለዚያ÷ ያልገመትናቸው ፍጡሮች "ያላወቁ አዋቂዎች" ብለው ይሳለቁብናል:: ψ